# Advice for people with water tanks living in bushfire-affected areas

# በጫካ እሳት በተጎዱ ቦታዎች ከውሃ ማጠራቀሚያ ጋር ለሚኖሩ ሰዎች ምክር

Amharic

## መግቢያ

የጫካ እሳት ብዛት ያለው ጢስና አመድ እንደሚፈጥር ነው። ታዲያ በጫካ እሳት በተጎዱ ቦታዎች ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ በዝናብ አማካኝነት የሞተ እንስሳት ወይም የጣራ ፍርስራሽና አመድ ታጥቦ ወደ የርስዎ የዝናብ ውሃ ማጠራቀሚያ በመግባት ሊበክል እንደሚችል ማወቅ አለብዎ።

እንዲሁም አመዱና ስብርባሪው በሚጠጡት ውሃ ውስጥ ሊገቡ ስለሚችሉና ጎጂ የሆኑ ኬሚካሎችን ስለሚይዙ ችግር ላይ ይጥላሉ። ማንኛውም የሞተ እንስሳ ውሃን እንደሚበክል ግልጽ ሲሆን ታዲያ ውሃውን መጠጣቱ ጤናማ አይደለም።

በቤት ጣራዎ ላይ ስብርባሪና አመድ መኖር የሚያሳየው የመጀመሪያ እጣቢ ውሃ ለመጠጣት ተስማሚ እንዳልሆነ ነው። የቤት ጣራዎን በቱቦ ውሃ ካፈሰሱበት ወይም ዝናብ ከዘነበ እነዚህ መርዛማ ነገሮች ታጥበው ወደ ውሃ ማጠራቀሚያዎ ሊገቡ ይችላሉ።

## ስለውሃ መያዣ ቦታዎች

ዝናብ ከዘነበ በኋላ ተመሳሳይ ነገሮች በውሃ መገደቢያ ቦታዎች ላይ ይከሰታል። ፍርስራሽ ታጥቦ ወደ ኩሬዎችና ምንጮች ውስጥ ይገባል። ስለዚህ በኩሬና በምንጮች ላይ ያለ ውሃ ለመጤጥ ተስማሚ አይደለም። ከነዚህ ምንጮች የሚወጣ ውሃ እንክብካቤ ካልተደረገበት በምንም መንገድ ለመጠጥ መጠቀም አይኖርበትም። ጥልቀት ካለው ጉድጓድ የሚወጣ ውሃ ለሰው ልጅ መጠጥ ፍጆታ መቀጠል ይኖርበታል። ለመጠጥ የማያገለግል ውሃ ምናልባት ለሌላ ጉዳይ መዋል ይችላል ማለት እንደ የእሳት ማጥፊያ ወይም ለአትክልት ማጠጫ ውሃ ሊሆን ሲችል ነገር ግን እንስሳት እንዲጠጡት አለመስጠት ነው።

## የዝናብ ውሃ ማጠራቀሚያ በጫካ እሳት መበከል ለመቀነስ ምን ማድረግ እችላለሁ?

በቤት ጣራውና በማጠራቀሚያው መካከል ላይ ለመጀመሪያ ፍሳሽ አቅጣጫ ቀያሪ በመግጠም ውሃን የሚበክል አመድና ፍርስራሽ የያዘ ውሃን ወደ ማጠራቀሚያው እንዳይገባ ለመከላከል ይቻላል። እነዚህ በአብዛኛው የህንጻ መሳሪያ መደብሮች ውስጥና በዝናብ ውሃ ማጠራቀሚያ አቅራቢዎች በኩል ይቀርባል።

## ከጫካ እሳት በኋላ የውሃ ማጠራቀሚያየ ከተበከለ እንዴት አውቃለሁ?

አብዛኛውን በርስዎ ማጠራቀሚያ ውስጥ ያለ ውሃ ምን እንደሚመስልና ጣእም እንዳለው ማወቁ የበለጠ መመሪያ ይሆናል።

- ውሃው ያልተለመደ ጣእም ወይም ሽታ ካለው ወይም ያልተለመደ ቀለምና ደብዘዝ ካለ ወይም የሆኑ ነገሮች ካሉበት ተበክሏል ማለት ነው። ታዲያ የውሃ ማጠራቀሚያው እስኪጸዳ ድረስና በሌላ አዲስ የዝናብ ውሃ እስኪሞላ ድረስ ወይንም በማጠራቀሚያው ንጹህ ውሃ እስኪሞላ ድረስ የነበረን ውሃ ለመጠጥ፣ ምግብ ለማዘጋጀ ወይም በረዶ ለመሥሪያ አትጠቀሙበት።
- በማጠራቀሚያው ያለው ውሃ ተበክሏል ብለው ከተጠራጠሩ።
- ውሃውን ለመጠጥ መጠቀም ከወሰኑ ታዲያ ከዚያ በፊት ከማጠራቀሚያ ያለው ውሃ እንዲመረመር ማድረግ (ከኬሚካል/chemical፣ ከጥቃቅን ህዋሳት/ microbiological እና ከአልጌ/ algae መጠን) ።
- ለመጠጥ ተስማሚ ያልሆነ ውሃ ለሌላ ጉዳይ ሊጠቅም ይችላል ማለት እንደ የእሳት ማጥፊያ ወይም የአትክልት ቦታን ለረማጠጣት ሲሆን ነገር ግን እንሰሳት እንዲጠጡት አይስጧቸው።

## የዝናብ ማጠራቀሚያየን ውሃ እንደገና ለመጠጥ መጠቀም የምችለው መቼ ነው?

- የርስዎን ማጠራቀሚያ ማጽዳት ቢያስፈልግ ወይም ባያስፈልግ ታዲያ ብፍርስራሽ የበከለ ውሃ ወደ ማጠራቀሚያው እንዳይገባ ለመከላከል የቤቱን ጣሪያ ማጽዳት ያስፈልግዎታል። ማንኛውንም ፍርስራሽ ከመጠጥ ውሃ ማጠራቀሚያው ለማስወገድ በዝናብ ውሃ ማጠራቀሚያዎ የመጀመሪያውን እጣቢ ውሃ አቅጣጫ ቀያሪ መሳሪያ መጠቀም ይሆናል። የመጀመሪያውን እጣቢ ውሃ አቅጣጫ ቀያሪ መሳሪያ ከሌለዎት ጣሪያው ከፍርስራሹ እስኪጸዳ ድረስ ከጣሪያ ላይ ያለውን የማጠራቀሚያ መገናኛ መቁረጥ ይሆናል።
- ዝናብ ከመዝነቡ በፊት በጣሪያውና በአሸንዳዎች ያሉትን ፍርስራሾች ማጽዳት ይሆናል። አደጋ እንዳይደርስብዎ ይጠንቀቁ።
- በአሸንዳው ላይ ያሉትን የሞቱ ወፎች ወይም ሌሎች ትናንሽ እንስሳት ጓንት አጥልቆ ማንሳትና ወደ ፕላስቲክ ለመጣል በከረጢት ውስጥ ማሸግ ይሆናል።

Department of Human Services

A Victorian Government initiative

State Government Victoria

- ማጠራቀሚያውን ሲያጸዱ አተላ/ወፍራም ጭቃ ካል ማንሳትና ውስጡን በቤት ውስጥ ማጠቢያ ኬሚካል (በመመሪያው ላይ ባለው መግለጫ መሰረት) ማለቅለቅ/መፈግፈግ ይሆናል። በማጠራቀሚያ ጋን ውስጥ ጥሩ የአየር መዘዋወር መኖሩን ሳያረጋግጡ መንጠላጠሉ በሚቀርቡ ቁጥር በአስቸኳይ ለአደጋ መጋለጥ ይችላሉ።

## በበለጠ መረጃ ለማግኘት

- የሚቀርብልዎን የመጠጥ ውሃ በማያሰጋና ጤናማ በሆነ ለመያዝ ማለስ ስለ ውሃን በክሎሪን ጀርሞችን ማስወገድ ምክር ያዘለ መረጃ የግልዎ መጠጥ ውሃ አቅርቦት በሚለው ጥራዝ ወረቀት ላይ ቀርቧል። እንዲሁም ከሚከተለው ድረገጽ ላይ ማግኘት ይቻላል: www.health.vic.gov.au/environment/water/tanks.htm
- የዚህ ጥራዝ ወረቀት ቅጂዎች በሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ የክልላዊ ጽህፈት ቤቶች፣ ምክር ቤቶች፣ ማህበረሰብ ማእከላትና በጫካ እሳት ማገገሚያ ማእከላት በኩል ይቀርባሉ።
- ስለውሃ ማጠራቀሚያ አጠቃላይ የሆነ ምክር በድረገጽ: www.health.vic.gov.au/foodsafety/issues.htm#water_carting_guidelines_ ላይ ይገኛል።
- በጋን ያለን የውሃ ናሙና መመርመር የሚቻልበት ላቦራቶሪ ለማግኘት በተሌፎን ማውጫ ውስጥ 'Analysts/ተንታኞች' የንግድ ሥራ በሚለው ስር ያለውን ማየት።
- ስለሞቱ ወፎችንና ሌሎች ትናንሽ እንስሳት ማስወገድ በበለጠ ምክር ለማግኘት የአካባቢዎን ምክር ቤት፣ የአካባቢያዊ ጠና ክፍልን ማነጋገር ይሆናል።
- ከእሳት ቃጠሎ በኋላ ስለርስዎ የዝናብ ውሃ ማጠራቀሚያ ጥራት በተመለከተ ለበለጠ የጤና መረጃ ለማግኘት በስብ አዊ አገልግሎት መምሪያ የአካባቢን የጤና ክፍል በስልክ 1300 761 874 ደውሎ ማነጋገር ነው።
- ከጫካ እሳት ጢስ እና ከህዝብ ጤና ማለት በንብረትዎ ላይ አደገኛ ሁኔታን ያካተተ ጋር በተያያዘ ሌላ እውነታ ወረቀቶች ማለት ከጫካ እሳት ቃጠሎና ጢስ በኋላ እንዲሁም የርስዎን ጤንነት ይሆናል።

ሁለቱም የእውነታ ወረቀቶችን ለማግኘት ዌብሳይት:

www.health.vic.gov.au/environment/emergency_mgmnt/index.htm#bushfires

ላይ ይገኛል ወይም በፖስታ ለሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ ለአካባቢ የጤና ክፍል መላክ ወይም በቁጥር 1300 761 874 ደውሎ ማግኘት ነው።

በሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ የአካባቢና ጤና ጥበቃ ክፍል በኩል የታተመ ቀን:

ጥቅምት/October 2006 ዓ.ም

State Government Victoria Department of Human Services